http://ethioliberty.wordpress.com/

H
YFU
TAFA-
YA



http://ethioliberty.wordpress.com/

ሰይፉ:መታፈሪያ:ፍሬው:

ውስጠት

ውስጠት

ከ

ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
፲፱፻፹፩

http://ethioliberty.wordpress.com/

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
Kurraz Publishing Agency

ስልክ / Tel. 11 27 19

ፖስታ ሣ. ቁ. / P. O. Box 30933

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ADDIS ABABA
Ethiopia

D
AMH
1Q

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ።
All Rights Reserved

የሽፋን ሥዕል — ሉቃስ አማረ

በቦሌ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ማ ው ጫ

ርእሶቹ ገጾቹ

ርእሱን አስመልክቶ 9

1979

* * ታኅሣሥ ...

- ልዩ—'ቃ 12
- ያብሮ አብሮነት ጉዞ 13
- ሰባ ሰማኒያ 17
- በራሳጅ ቡና ቤት 19
- የሕይወት ፍጥርቅታ 21
- ነገር 24

1978

* * ነሐሴ ...

- ተፈጥሮ ብልጠቱዋ 25
- ያመሻሽ—ወርቅ 28
- ወዲያ—ወዲህ 29

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሐምሌ ...

ገጽ

- ብርቃማሞች 30

* *

ሰኔ ...

- የተፈጥሮ ባላደራ 31
- ልጃገረድ 32
- ምሾት 35
- የጊያኖ ላይ ምጥ 36
- ዘራሰብ ጥያቄው 37

* *

ግንቦት ...

- ያመሻሸ ፍለጋ 39
- የፍቅር ዐይነት 40
- ዘላለምን ባብሮነት 41
- የፍጻሜው ባላደራ 42
- ከረምት 46
- ዘላለማለምን በግር 47
- ያንድ ሥልጣኔ ታሪክ 48
- ተፈጥሮ ፍራቱዋ 50
- ፍቅር ገዳይ 51
- መሥፈሪያ 52
- ሙሾ ላማይጨስ ሞዛርት 53
- እንግዳዪት 54
- ጉልበተኛ የፈጠራት ዓለም 55
- የሂደት ዐይነት 56
- የፍቅር ጥያቄ 57
- ያንድ አቅጣጫ ጩኸት 58

* *

ጎዳር ...

- ከሥፍር ባሻገር 59
  1977

* *

ነሐሴ ...

- እርካታ 60
- ኮዳ ቦጭ ቦጭ 61
- የቦታ ጥያቄ 62

* *

ሐምሌ ...

- ምርጫ ያለው ይመስል 64
- ድጉልጉል ደመና 65
- ቀለም ድምቄ 66
- የዘመድ እንግዳ 68

* *

http://ethioliberty.wordpress.com/

* *

ግንቦት ...

- የዘራሰብ ጥገኛ 69
- ሕይወት በተዘርዝሮዋ 72
- ምኞት በዕራቁ 73
- ማንሜነት 74
- ምኒልክ ሐውልቱ 75

* *

ጥር

- ሰው 78

በተለይ

ለ

አሚ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ርእሱን አስመልክቶ

ውስጠት ምን ቃል ነው? ምንስ ማለት ነው? እሱንስ አስመልክቶ ምን ምን የሐሳብ ዐይነቶች ማንሣት ይቻላል? የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ በሚቀጥሉት አንቀጾች ውስጥ እሰጣለሁ ።

የውስጠት ሥርወቃል ወሰጠ የሚለው ግዕዝ ቃል ነው ፤ ቅርጹ ወይም አፍአዊ የቃል መልኩ ግን ፣ ግዕዝም አማርኛም ነው ። እንዲህ መሆኑንም ፣ ቃሉ አንደኛ 'ምሕረት' ፣ 'ሥርጸት'ና ወዘተ... ከሚሉት የግዕዝ ቃላት ጋርና ፤ ሁለተኛ 'ቅብጠት' ፣ 'ክብደት'ና ወዘተ.ከሚሉት አማርኛ ቃላት ጋር የሚያሳየው ተመሳስሎ ያረጋግጥልናል ።ስለዚህ ፣ ይህ ቃል ፣ በምላተ-ቅርጹ ፣ ከሁለቱ ቋዋንቋዎች መልክ አሻርፎ አካል ያበጀ አዲስ ቃል ነው ።

ትርጉሙ ደግሞ እንዲህ ነው ። ወሰጠ 'በውስጥ መሆን ... ወደ ውስጥ መግባት ፣ መክበብ ፣ ማማከል' ማለት እንደሆነ መጽሐፈ ሰዋስው ወዘተ ይነግረናል ። ከዚህም የተነሣ ፣ ውስጠት የሚለው ቃል ፍቺ ፣ ከወሰጠ ጋር የተያያዘ መሆን እንዳለበት ግልጥ ነው ።

በዚህ ዝምድና መሠረት ፣ ውስጠት 'ይዘት' ማለት ነው ሊባል ይቻል ነበር ፤ ነገር ግን ፣ እኔ እንዳሰብኩት የውስጠት ምላተ-ትርጉም ፣ 'ይዘት' በሚለው ላይ የሚጨምረው ነገር አለው ። ይህን ጭማሪ ፣ 'ጠላ—እንኮላ' ወይም 'ያንኮላ ውስጥ ጠላ' በሚል ምሳሌ እገልጻለሁ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

እንደሚታወቀው ፣ 'ይዘቱ' ጠላው ብቻ ነው ፤ አንኮላው መያዢያው ነው ። ውስጠት ስል ግን ፣ ጠላውን ፣ አንኮላውንና ፣ የሁለቱን አንዱ በሌላው ውስጥ ሆኖ መገኘትንም ይጨምራል ። እና ውስጠት በ'ይዘት' ላይ የሚጨምረው ፣ አንኮላ ፣ ጠላ ፣ እያሉ አንዳንዱን በመጥራት ወይም በማሰብ ፈንታ ፣ ሁለቱንም በተዋ ስጠ ፣ ወይም በተዋወጠ ማሰብን ነው ።

ለእኔ እንደ መሰለኝ ፣ በግጥማዊ የነገር ምልከታ ፣ 'ይዘትና ውስጠት' ልዩነት አላቸው ። ይህንንም ለማ ሳየት ፣ 'ይዘት' የሚለውን ትቼ ፣ ውስጠት እሚለው እንግዳ ቃል ላይ ብቻ አተኩራለሁ ። ትኩረቴም ፣ ከፍ ብዬ ፣ 'ርእሱን አስመልክቶ ምን ምን የሐሳብ ዐይነቶች ማንሣት ይቻላል?' ላልኩት ጥያቄ መልስ ይሆናል ። በዚህ መልክ አራት ሐሳቦችን አነሣለሁ ።

አንደኛ ፣ ውስጠትነት የዓላማችን መሠረታዊና ቁዋሚ መልክ ነው ። ለዚህም ፣ ባንድ በኩል ፣ የሴሎችንና የሕይወትን ፣ የመብልዕንና የአካልን ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ፣ የፅንስንና የማሕፀንን ፣ የሰውንና የአንጎት ማስገቢያውን በጣም ሲርቅ ደግሞ ፣ የዩኒቨርስንና የምላተ - ይዘቱን የግንኙነት ወይም የተዋስጦ ዐይነቶችን በምሳሌነት ማምጣት ይቻላል ።

ሁለተኛ ፣ መጨረሻ ካነሣሁት ከዩኒቨርስ ነኩ ጉዳይ ጋር ተያይዞ አንድ በሐሳቤ የሚመላለስ ዐይነልቦናዊ ርጉየት አለ ። ይኸውም እንዲህ ነው ።

ከላይ ከላይ ጎበብ ያለ የሚመስለው ሰማይ እንደ ጣሪያ ፣ ከታች እታች ደግሞ ፣ ሁሌ ሂዶ ሂዶ አድማስ

ሲደርስ በተዳፎት ወደዚያ በኩል ከምበል የሚል የሚመስለው መሬት ወለል ሆኖ ፣ ትልቅ ትልቅ አዳራሽ ይፈጠራል ። ከዚህ አዳራሽ ውስጥ ከሚገኙት የተካቶ ዐይነቶች መካከል ፣ በቀደምትነትና በትኩረት ሊታሰብ ይገባዋል እምለው ሰው ነው ።

ይህም የርእየት ዐይነት እየጋበዛቸው ፣ ሰውና ሰው ፣ ሰውና ተፈጥሮ እና ሰውና አዳራሹ የሚሉት ልዩ ልዩ የምልከታ ርእሶች አልፈው አልፈው በሐሳቤ ይመጣሉ ። ለምሳሌ ፣ 'ሰማይ - መሬቱ ተካድኖ ያ ተካድኖ አዳራሽ ሆኖ እና ወዘተ . . .' ብሎ የሚጀምር አንድ ግጥሚም እንደዚህ ያለው የሐሳብ ዐይነት ግፊት ነው ።

ሦስተኛዉ ፣ የዚህና የመሰል ተጽዕኖ ዐይነቶች ውጤት ሆኖ ፣ የውስጠት ሐሳብ እዚህ በቀረቡት ግጥሞች ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ፣ ይበልጥ የሚደጋገምና ፣ ከሁሉም ዋና ሆኖ የሚገኝ የሐሳብ አቀራረብ ስልት ነው ። ውስጠት በርእስነት ከመጣባቸውም ምክንያቶች ዋናው ይኸው ነው ።

አራተኛና መጨረሻ ፣ ውስጠት በቀላሉ የሚረዱት ቃል አለመሆኑ ያሳዝናል ፣ ግን ምን ይደረግ ፣ እዚህ የሰጠሁትን ትርጉም ሊገልጽልኝ የሚችል እሱ ስለ መሰለኝ ፣ በክብደት - ቅለት ምክንያት በሌላ ቃል ልለው ጠው አልፈለግሁም ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ልዩ—ነቃ

የወርቅ ቀለበት
ልሙጥ ።

ፍቅር ንክር
ከቡር ።

ልዩ—ነቃ
የጌጦች አለቃ ።

ምሥጢር ገላጭ
ልብ አስደንጋጭ ።

አንዲት የሕይወት ቁራጭ
ቁራሽ
ከኮረብታ ደረት ፍራሽ ፤
ብዙ ዓመታት የኖረች
ዕድሜያማ
ያንድ የኑሮ መልክ ማማ ።

እሱዋ ቁራጭ
የከፍራቹ
ቁጭ
ጭጭ
ሥስትየዋን ።

ማለት
አንዲት ጎጆ
ያረጀች ፥
አጠገቡዋ አንድ ዛፍ
ወይራ
ሽበት የወረረው ቅርንጫፍ ።

ከዚያን የሆኑ ሽማግሌ
አዛውንት
ባለ መቶ ምናልባት
ከመቶም በላይ ዓመታት ።
ከጎጆዋና ከዛፉ ማሕል
ቁጭ ብለዋል ፡—
ቁጭ

ጭጭ ።

• •

የተከሉት እራሳቸው ናቸው
ዛፉን
ዱሮ ዱሮ ፤
ጎጆዋም ትዳር የጀመሩባት
ኑሮ
የሃያ ዓመት ልጅ ሆነው
የዚያ ግማሽ ከሩብ
ሙሽራቸው ።
እና ጎናንባቸው
ይቺው ጎጆ
የጋብቻቸው መዋጮ
በዚያች ምሽታቸው
የጫጉላ
የመዋደዳቸው መላ ።

• •

http://ethioliberty.wordpress.com/

ማዶውን ሌላ ኮረብታ ነው
ከለላ —ሥ ርጋው
ጀምበር
ላዳር ደርደሬ
ባጭለምልምነቱዋ አስፈሬ ።

• •

የኮረብታውም ረዥም ጥላ
ወረድረድ
ተቆልቆል
ሜዳውን ጨርሱዋል
ደረታማ ዳገቱን ተያይዙዋል ።

• •

አሁን ሦስት እሩቡን ወጥቶ
ያንን ዳገት
ከግር ፣ ጫማቸው ላይ ተኝቶ
እያቀዘቀዛቸው ነው ያለ ፣
ቀስ በቀስ ሊጎናንባቸው
እንደዚያች ጎጁዋቸው
እሱዋንም ጨምሮ
ያረጀ ዛፉንም አብሮ
ሊያረጋቸው
በረዶ—ረዶ—ረዶ
ላብሮ አብሮነት ጉዙዋቸው ።
ወዴ ሕይወት ወዲያ በኩል ።

• •

http://ethioliberty.wordpress.com/

እና ይሄ ሁሉ ሲሆን
እሳቸው
አገጫቸውን ዐረፍ
በጉልበትና ጉልበታቸው ደገፍ
እና ዐቀፍቀፍ
በጆቻቸው
ሁለት ቅልጥሞቻቸውን
ዐሥሩ ጣቶቻቸው ወርደው
ከሌሎቹ ዐሥር ተጋምደው
ይጨዋወታሉ ጨዋታ
የቤተሰብ
ያለፈ ትዝታ መሰብሰብ ።

• ሰባ ሰማኒያ

እንዴት—እንዴት! እንዴት ሙዋሸሸ
አበባ!
የሁዋሊት ሁዋሊቱን ሸሸ
ውስጠትሽ
ሽብሽብ ብሎ ቀረ
ቆዳሽ
የፊትሽ
እንዲያ ሙሉ የነበር ፥ እንዲያ ሙሉ
የልጅነትሽ ፀዳሉ ።

• •

እይው አስቲ ሲመሰክር
እያሞካሸሽ
የኛ የልጅነት ዘመን ምስልሽ ።
ማን ኮረዳ ነብረሽ ነበር ይላል
አሁን
ቢነግሩት ያምናል
የኒያን ዓመታት መልክሽን ያያል
ባይነልቦናው
እርጅና ያጠፋውን ያጤናል!?

• •

ያንን ያይንና—› ፍንጫ ረቂቅነት
የልጅነትና የውበት ጥምረት ፤
ጥንፍፍ አርገን በላነው ፤ ጥንፍፍ አርገን

http://ethioliberty.wordpress.com/

እንደሱ አርገን ጠጣነው
ልጅነቱንም
ረቂቅነቱንም
ውበቱንም
ወደ—'ንጀራና ወተት እየለወጥነው ።

• •

የዚያ-'ዚያ ውጤት ሆኖት
አሁን
እይው!
የኛን የልጆችሽን አባቶች መሆን
እንዲህ በዙሪያሽ ቆመነው
እየፈራነው የማይቀረውን እየፈራነው ።

• •

• በራሳጅ ዙና ዜት

ኮረፈፈፍ—ፈፈፍ—
ካፌ
ቡና ኮረፌ ።

• •

ጮሮሮሮር
ፈሳሽ ክር
ገመድ
ሲወርድ
እየተጥቆረቆረ ።

• •

እና ሲወረወር
ሲዋደድ
ውሂዝ
ከጥጥር ።
ማለዳ ማለዳ
ቁርስ ዕዳ ።

• •

ያው መጣ
ኮረፌ
ትኩሳት ላፌ !
ታጅቦ
በሦስ'—ማዘን
ወይም በክቡ

ድብድቡ
ቡና አጎዳኝ ምግብ ።

• •

መሮጥ ነው
ከዚያን
እያቆለማመጡ
አፍ
ቁልቁል መጫን
የጉሮሮን ላይ
ከደቂቃዎች እሽቅድምድም ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• የሕይወት ፍጥርቅታ

የጎማና አስፋልት ማሕል ፍጭት
ሕይወት ዕንቀት
ዱቄት ፤
ድርስ ሆነና ፣ ሆነና ድርስ
ባባ ፈጣን ጎዳና ፣ ባባ በራሪ ፡-
እሱ አሽከርካሪ
አሩዋሩዋጭ
ሕይወት እፊት እፊቱ አምላጭ ።

• •

በጎማና አስፋልት ተጋግዞ
ሕያውን እዚያ መሐል ይዞ

ድፍጥጥ!
በመብረቅ ፍጥነት
ፍርጥርጥ ፤
ሕይወት ሎሚ
ፍሬውን ይመስል ፍጥርቅ ፤
እና እዲዮስ !
አንቺ የጠፋሽ ሕይወት አዲዮስ!

• •

ከዚያንንም ትከዝ!
ትከዝ ጌታ ሞት

http://ethioliberty.wordpress.com/

ግርግሩ ማሕል ቆሞት ፡
እራሱን በራሱ እያጽናና
እያባበለ
እና እያለ፡-
ቻለው!
ለዘላለማለሙ ቻለው !

• •

ምክንያቱም
እንዲህ እየተደፈጣጠጠ
አንጀት - ጉበት እየተመጣጠጠ
ባንተ ነው እሚያሳብቡ — ባንተ!
ኩኩ - መለኮቴ ስሙ
የዘራሰብ ሕመሙ
የተሳሳተ ሮሮው
ሰው እኔን መሆኑን ባወቀው ።

• •

እና የኔውም ይሄ ነው
ይሄ ነው ዶሴዬ ይሄ ነው ፡-
ገላጭ ዳኛ እማይገኝለት
ይሄ ነው ክሴ ይሄ ነው
የሚሊዮና ሚሊዮን ዓመታት ቅርሴ
ሰብአዊ አባዜ ፡
በባዶ ሜዳ ፡ ባዶ ሜዳ ትካዜ ።

• •

እና ምናለ ፡ ከዚያ ወዲያማ ምናለ
ሕቅ — ድርቅ
የተገጨው አስፋልቱ መሰለ
በተቅላልት ስለ ተበከለ ።

• •

ሕቅ—ድርቄማ ፡ ሕቅ—ድርቁ
ስቅቂ
ዐይኖቹ ቡዝዝ
በበድንነት ሁኔታቸው ፍዝዝ
ሐሳብ የገባቸው ይመስል
በሞት ዓለም ሆነው ማሰላሰል
የሕይወትን ጉዳይ ማውጠንጠን
ያለፈን የኑሮ መልክ ማተኮር ።

• •

ዐይኖቹ በፍጠት
በድርቀት
መሰሉ
እሚ ያስተውሉ ፤
ትክ ብለው
በነሱ መስኩትነት ተፈጥሮታ
ሕይወት
እንደ ተተኮሰ—ፅዕታ ፤

መፍ—ብረቱዋን ስትበር የተከተሉዋት
ባይናቸው

በድን ትክታቸው
በተለያየን ፤ ተለያየን ፤ ተለያየናቸው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• ነገር

ትንሽ የነገር ድንጋይ
ድቡልቡል
መዳ ሥጋ ትመስል
ሄዳ ሄዳ ቅርቅር
ከጉሮሮና ጉሮሮ ማሕል፡-
ስሚት የማሳመም ሥራ
ውስጠት ቡርቦራ ።
ነወደ ልብ ነው የመጣችው
ሽቅብ ፤
እና ሄዳ ገባችው
ከጭንቅላት
መቼ—እንደምቶጣ—ንጃላት ።

• ተፈጥሮ ብልጠቱዋ

አንዱም ፣ አንዱም ፣ አንዱም ፣ አንዱም
የነጠላዎች ድግምግም
ተዳምሮ
ከምርምር ምላተ—አካል ቀምሮ
የተፈጥሮ ፣ ተፈጥሮ ፣ ተፈጥሮ ።

• •

ተዳምሮዎቹዋ እኛ
ተካቶዎቹዋ
የፅንስ—ፅንስ ፅንሶቹዋ ፡
አካታች ማሕፀናችንም እሱዋ
እናታችን ፤
ተፈጥሮ መርቃችን
በሕይወት ሂደት አጉዋጉዋዥ ጀልባችን ።

• •

ነጠላ ፣ ለንጥል እራሱ ሲያስብ
ተፈጥሮ ለምላተ—አካሉዋ መጠበብ ፤
በንዲያ—ንዲያ መጠበብን ተጠበበች
ለተካቶዎቹዋ
ለተዳምሮዎቹዋ
ለኛ ለማሕፀኑዋ ውስጥ ተቋዋጥሮዎች
እራሱዋን በራሱዋ እየጠየቀች ።

• •

እንደ ምን ብሎ ላበባነት ይደርሳል
ይበስላል
ለፍሬነት ይበቃል ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ዘራፀሞት·
በድንገት ሂደቱ ከመቀጨት ይደርሳል
ማልዶ?
እንደ ምን ብሎ ያቆጠቆጠ ሁሉ ይመርታል ?
ባዝራ ድንጉላዋ ሲቦርቅ ይታየታል
ሳይሞትባት ?

ተረግዞ የተወለደ ሁሉ ያድግላታል ?
ዘራንሰላት ?

እሱ—'ሱን እያሰበች እስ—'ሱን
ተጠበበች

ለሕይወት መቀጠል ዋስትና ፈለገች ፤
እና ይኸውና
ያገኘችው ዋስትና
(ብልጥ አይደለች) ።

• •

ዱሮ ዱሮ የሆነ ነው አሉ
ሲያወሩ
የጥበብ ሥራ ነበር እያሉ
የተፈጥሮ ።

ታዲያንን እሱዋ ታዲያንን
ከሆነ በረሃ የሆነ ሥር ምሳ
በዚያ በሥሩ የሸሉን ማይ ጠቅሳ
አቀመሰቻቸው አሉ
ለወላጆቹ
ከሥሩ በዛ ያለውን ለናቲቱ አጉርሳ ።
ለዚህም ነው እናቶች ተፈጥሮን የሚከሱ
ሁሌ

ባድላዊነት ስሙዋን እያነሡ ።

• •

ለማንኛቸውም
ተፈጥሮ
በዚህ ወላጅን በልጅ—ፍቅር ለከፈች
ነደፈች
ጠነወተች
አሳበደች
እናትና—'ባትን የልጅ ባሮች አረገች ።
ከምንት በላይ የሆኑ ባላደራዎች ፈጠረች
ለሕይወት
ለንክብካቤዋ
የዘላለማለም ዋቢዎቹዋ ።

• •

ተፈጥሮ ይህን ስሜት ሠርፃ
በወላጆች
ውስጥ ውስጡዋን እየሣቀች
ባቁዋጠረችው
ወደ ሌላ ሥራዋ ሂደችው
ልቡዋ ዐርፎ
አቁዋጥሮዋ እግይፈታ ጥያቄን አትርፎ ።
ለሰው ለራሱ
ግዙ ለሕይወት—'ንቆቅልሽ ግጡ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• ያመሻሽ ወርቅ

እምንተዋወቅ መሰለኝ እምንተዋወቅ
አንቺ የጥልቀት ጅምበር
ፍጠት ፍልቅቅ
ተቅላሎት ድምቅ
ያቴና ተራሮች አድማስ ፣ ያመሻሽ ወርቅ ።
ርቀት መጠች ጮራዎችሽ
ርችቶችሽ
ርጭቶችሽ
አሸን ምጣትሽ
ተብጫርጫት ቅልቅል ተቅላሎትሽ ።
በነሱ ተቅለመለመው
ያውሮፕላን ማረፊያ አካባቢው ።
ትራንዚት :-
ጉዞ ለመቀጠል ጉዞ
እያልኩ በካሁን—አሁን
ሊንቀሳቀስ ፣ በረራውን ሊጀምር ቆመነው ።

• ወዲያ—ወዲህ

"ከዚህ ዓለም—ከዚህ—ከዚህ ዓለም" ይላሉ
ይህን ዓለም ሞልቶት ኖሮ እንዴ ነበረ ሁሉ ።
ከጥቂት ወዲያ—ወዲህ ያላለፈ
እሱ ለራሱ ፤
እና የሀዋላ ሀዋላ የተቀሰፈ
ተጨርሶ
እሆነ አጋጣሚ ላይ ተከስክሶ ።
"ወደዚያኛው ዓለም—ወደዚያኛው" ይላሉ
ደሞ
ባስታሞ የኖረ ባስታሞ
ዕለትን በለት እየገፋ
የዚህን ዓለም ችግር በወዲያኛው ዓለም ተስፋ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• ብርቃማሞች

ጉዋዳማ ሣር ቤት ጉዋዳማ
ያዘለች እናት ።
ብርት ብርት ነገሮች የያዘቱ
ሁለቱም ፡-
ሕይወት አድን አንጀራ
ጉዋዳማዋ ቤት
ሕይወት ያለው ልጅ
በጀርባዋ አዛይዋ እናት ፤
ከለት—ለት ተሸጋግሮ ሕይወት ።

• የተፈጥሮ ባላደራ

ሰሞኑን ተበልቶ የነበረውን ይመስል
ሙት እህል ፤
የዚያን ያህል እንኩዋን ትዝ እማይል
ጣዕሙን ረስታዋለች
ድካሙን ብቻ ይዛ የቀረች
የተፈጥሮ ባላደራ
ሕይወትን የማስቀጠል ፤ ማስቀጠል ሥራ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• ልጃገረድ

የፊት እንጥልጥላት የፊት
እምባ—'ርግዛት
እየተገፋ ሽቅብ
ከረጢቱዋ
የምባዋ
በሆዱዋ መደብደብ
ሥውር ሰበብ ።

• •

የራስ—በራሱዋ ቅራኔ
ያለሁ—የለሁም ብያኔ ፡-
ውጪት ሆነና ውጪት
ያወዳደቅ
ከጉርብጥብጥ መሬት
ጉዝጉዋዝ
የተፈጥሮ ባሕርይ መዘዝ ።

• •

በዚሁ—እዚሁ—ተገዘገዘች
ስለዚሁ
ውስጡዋን
ገና ድብቁዋን እያለች ፤
እያስያዘች
እራስዋን እየከሰሰች በራስዋ
ለጎብረተሰቡ ፍርዱዋ ።

• •

በቀደም—'ለት
ሳያት
ብቻዋን
ነበረች
በንዲያ—'ንዲያ እየሄደች
ጎዳና ፤
እና እየሰነጠቀች
የሕዝብ ብዛት
በፊት እንጥልጥላት
እምባ—'ርግዛት ።

• •

ወዲያውም እያሰማች
ኦርኬስትራ
የውስጡዋ ተናውጦ ዝየራ
ያመፅ ቃና የነበረው ሥራ ።

• •

ሥጋ—አባላቱዋም ደም
እንዳሉ
ተከትለው
የኦርኬስትራውን ቅኝት
ወገን ለይተው
ከሁለት
በንጃልሽ እንጃልሽ ጠባቸው
ስትሄደው
ድምፃቸው ፡—
አለንም—የለንም
አለንም—የለንም

http://ethioliberty.wordpress.com/

አለንም—የለንም
አለንም—የለንም ።

• •

ምስኪን ልጃገረድ
ሴት ልጅ ሆኖ መወለድ ።

• ምኞት

እምሸለቅቀው ጠፋኝና—ነዊ እምሸለቅቀው
በሸለቀቅሁ
ሕይወት ወይነቱዋን ባወቅሁ
ቁዋሩዋን
አንኩዋሩዋን
ልበይነው እምችለው አካሉዋን
አስኩዋሉዋን
ግዘፈት—ከቅርፅ ያለው አካል እንዳላት
ለዚያውም
የዳበሳ ዕውቀት
ሥርዓት
ከሕያዋኑ ትርምስ የቅይጥይጣቸው ውስጣ ውስጥ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• የፒያኖ ላይ ምጥ

"ድን!" እየመለሰ ፤ እየመለሰ "ድን !"
"ድን ድን ! —ድን!" እና "ድን !"
አንዲቱዋን ኖታ ብቻ
መቧቻ
መጣሁ መጣሁ ለሚለው ዜማ መክፈቻ ።
ወይ ተከታትሎ አይመጣው
ዜማው
ተከታትሎ
ጎብራድሚፀን በጉልሀ አሰናስሎ ፤
ወይ አይቀረው
አይጠፋው
ጨርሶ
ታስቦ እንዳልነበረ ያህል ተደምስሶ
ካሳብ
በሆነ ሆነ ፤ ለምሳሌ ፤ በምቢያለኝ ሰበብ ።
ዕርፍ ብሎ እንዲቀመጥ ዕርፍ ብሎ
ሰው
በማይወጣው የስንክን ምጥ መሠቃየቱ ቀርቶ ።

• ዘራሰብ ጥያቄው

የትንሽ ልብ ውስጥ ድውድውታ
የሰው አካል ውስጥ ጨዋታ
ጭፈራ
የደም ማሰራጨት ሥራ ።

• •

የትንሽ መሬት ላይ መለስ ቀለስ
የሰው በሕይወት መንቀሳቀስ
ዕለት ለማግሥት
የቁጫጮች የምድር ላይ ኑዋሪነት ።

• •

ከዚያን ይቺ ትንሹዋ መሬት
እራሱዋ
ድቡልቡሌ
አዞሬ እንቁላሌ
የሰፈው ሕዋ ውስጥ እንዝርት
ሽክርክሬ
የዩኒቨርስ ትንሽ ልቡ መሰሌ ።

• •

መጨረሻውን ዩኒቨርስ እራሱ ፤ነው
እንዳላቸውን ያካተተው፡-
ልብና ሰውን
ሰውና መሬትን
መሬትና ሕዋን
ሕዋንና ሕዋ ፤ያካተታቸውን ምሥጢሮች

http://ethioliberty.wordpress.com/

የሰውን አእምሮ ሠርጓሪዎች
አጠያያቂዎች
መጣቂ—ጣቂ ኃይላትን ጋባዦች ።

• ያመሻሽ ፍለጋ

አንቺ ድብዝዝ ፡ ድብዝዝ
እኔ ድንግዝ
የት ይሆን መገናኛችን
ተፈጥሮ
ገጽ ለገጽ !? ፡—
ያመሻሽ ፍለጋ
እኔ ካንቺ ላወጋ
እነሆኝ ስመኝ
ተፈጥሮ
ውስጠቴ በሮ
ወዳንቺ
በሆነ ሆነ፡ ነገር ተሞርምሮ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• የፍቅር ዐይነት

በቁንጮ—ድመ·ጫ መዳራት ለመደና
የፍቅሩ መስፈሪያ ቁና
ባህላዊ የፍቅር ቃና ።
ይኸው ልምዱ አደገበት ይኸው ልምዱ
እኔ ወንዱ ባይ እኔ ወንዱ ።

• •

ቁንጮ—ድመ·ጫ ጥንው·ት !
ሰበበኛ ፍቅር ሰበበኛ
ሞት መጋኛ ።
ዕብድ ያበደ !

• •

ቁንጮ—ድመ·ጫ ልምዱ አለቅ ብሎት
"ወንዱ !"
ባንድ ጎዶሎ ቀን ባንድ ጎዶሎ
ፍቅረኛውን ገደለ
"ዘራፍ—ወንዱ !" ብሎ !

• •

እንዲያ ብሎ ገደለ
ልስልስ ገላ በሰላ ጩቤ አማሰለ ፥—
ደርሶ ገዳይነት
ጠላት ከሌለበት ፣ ከሌለበት ጀግንነት ።

• ዘላለም ባብሮነት

ሰማይን ተከናንበን
ጎባባውን
ምድርን ፈርሽን
ቦቄዋን
የኒያ ማሕል ተጋምዶዎች
እነሁዋችን
አንቺና—'ኒያችን
ተፈጥሮ
የዘላለማለሙ አብሮኞዎች ሆነን ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• የፍጻሜው ባላደራ

ጌታ ሞት እፈት—እፈት ፣ እፈት—እፈት
ሁዋላ ሁዋላው የቀባሪው ትመት ፡
ረመድመድ—ረመድመድ
ረመድመድ—ረመድመድ
ትመቱ
በጉዞ ቀብሩ ፣ ጉዞ ቀብሩ ፣ ጉዞው ፣
እና ሰተት—ተት—ተት
ሂደቱ
ቅጥልጥላቱ ፤
ጠጠር እያናናደ
ትስፍንጥር ተናንደውን አርቆ እየሰደደ ።

• •

ጉንዳን ትመት
ቀስ ያለ ፣ የእንቅስቃሴ ዐይነት ።
እና በዚያ የሂደት ዐይነት
ጌታ ሞት ፣ እፈት— እፈት ፣ እፈት—እፈት
ሁዋላ ሁዋላው የቀባሪው ትመት
ቅጥልጥላት
ያእላፍ እግር የትእልፈት ።
እና እሱ አእላፋቱ
ትእልፈቱ
በትመቱ
ብድግድግ—ድግድግ
ድግድግ—ብድግድግ
ብድግድግ—ድግድግ

ድግድግ—ብድግድግ
እግር ከመሬት እያነሣ መልሶ ሲያዋድድ
ቡልቅ—ቡልቄ ዐፈር ሲደቀድቅ ።

• •

እየቀሰቀሰ ቡልቅ—ቡልቅ ዐፈሩን እየቀሰቀሰ
እና እያቦነነ
እየጣሰሰው የሚሄደውን አየር አደመነ ፡-
እሱ ራሱም የደመና ውስጥ ትመት ሆነ ።
እና ከሩቅ ሲታየው
የሚለየው
የሆነ ሕያው ባሆነ ጉዞ ላይ እንዳለ ብቻ ነው
የቡልቅ—ቡልቄ ዐፈር ውስጥ ሲው ።

• •

እና እፈት—እፈት ጌታ ሞት እፈት—እፈት
በዚያ ጉዞ
ሁዋላ ሁዋላው የቀባሪ ትመት
ቅጥልጥላት፡-
ያንን ቡልቅ—ቡልቄ አቡዋራ ለብሶት
ተከናንቦት
የእስመ መሬት አንተው ወሬ
የቀባሪውና የጌታ ሞት የጎበረት ዝማሬ ።

• •

መሬት መሬት እያስተዋለ መሬት መሬት
እና ዝቅ ባለ ድምፅ ዝቅ ባለ
ሕምታም ጉርምርምታም በመሰለ

http://ethioliberty.wordpress.com/

እያለ ዘመረ
ትመቱ
ቅጥልጥላቱ
በዜማ ልውስውስ ታላቱ ፡-
"ያንቺን ላንቺ ተፈጥሮ"
"ተፈጥሮ ፡ ያንቺን ላንቺ"
ከነትርፋ ያመጣንልሽን ውስጂ

• •

እና ቀጠለ ጉዞው ፤ ጉዞው ቀጠለ
እየተግተለተለ
ትመቱ
ቅጥልጥላቱ

እየመራ ጌታ ሞት ፤ ጌታ ሞት እየመራ
እፊት—እፊት
ሁዋላ ሁዋላው የቀባሪው ትመት ።

• •

በሂደታቸው እየራቁ ፡ እየራቁ ፡
ተራሮች ዞረው ተራሮች ዘለቁ ፡-
እና ደረሱ ካንደኛው ጫፍ
ሊቀብሩበት ከተባለው አፋፍ
በዚያ ግርማማ ሌሊት ፡—
ጨረቃ ፍጠት
ከዋክብት ፍካት
በድን ጸጥታ ፤
በግርማ ሌሊት እንዲሆ ታስቦ ነው
ቀብሩ
ለሰውና መሬት ተዋስጦ ክብሩ

በምላተ—ፍጥረታት ምላተ—ትሕርት ፡-
ትክ !
መመልከት
የክቡር አስከሬኑን ግባ—ተመሬት ፡-
የመረካከብ ሥራት
የቀብሩ
የሕይወት አልባ አስከሬን ክብር
የተፈጥሮን ለተፈጥሮ የመመለስ ምሥጢር ።

• ክረምት

ክረምት ፡ ሐሉመ ፡ ሐሉመ
ዝናብ መጣ
ያመነ ፡
ያው ጥቁረቱ
ዛቻ እርጥበቱ
ሹዋ ብትን ገበያ ፡-
ጥድፊያ በጥድፊያ
ግፊያ
ላታላ ፍለጋ ፡ ላ—ፍለጋ ግልቢያ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• ዘላለማለምን በግር

ዘላለማለምን ሰንዋዙ ፡ ሰንዋዙ
የኔነት ዐይነቱን ያግዙ
ጨርሰው
እንዳልነበረ ያህሉን ትተው
ማንሚነትን ይላበሱ ።

• •

እና ይሄዱ ባሳብ እግር
ዓመታት መቁጠር
ዘላለማለምን እስኪያህል ማዳመር
እያዳመሩ ሂደት እያዳመሩ
ኑኃዘመንን ክኑኅፍኖት እያቁዋጠሩ ።

• •

እሩቅ ብእሲ ተቀላቅሎት
ከዘራሰብ
እና ተዳምሮት
ካሉት — ከሞቱት ስብስብ ።

• •

እና ተውጠት ነው ያለ ተውቦት
እዚያ ውስጥ
እሩቅ ብእሲ
ቅንጣት
በብሔረ — ዩኒቨርስ ነዋሪነት ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ትልቅ ትከሻ ፣ ትልቅ ጫንቃ
ልብስ የተደራረበበት ዕቃ ።
ደሞ ፣ ደሞ
በዚያው የተከፋፍሶ ስሚት ታሞ
ከራሱ ላይ ደመና
ጥቦ ንጣት
አውሮፓዊ ጉተና
ሆነና ጌጥ ሆነና
የዚያ የመካከለኛው ዘመናችው
በየበላይ — የበታች ተካሉዋችው
ድንበር
ባለቃ—ምንዝር
ጌታ —' ሽከር
አግብርት — አእማት መቁጠር
በጌታ —' መቢትነት
ወይም እመቤት ጌታነት ።

• •

በዚያን ዘመኑ ሥራት
ቁልቁል ሽቅብ መተያየት
እስከ ረኔሳንስ (ዳግም ልደት)
ያዲስ ፍልስፍና ፍልቀት ።

• •

ያ ፍልቀት ነው ያዳናቸው
ጉተና—አልባቸውን ሲያቆማቸው
ሸልቅቆ

ሰብአዊ ድክመታችውን አድምቆ ።
እና እኛ ያየነው
ያገኘነው
ያንን ጉተና አልባ እራሱን ነው ።
ባሰብ ፣ በጅቡቲ በኩል ሲመጣው
ያኔ
በዚያን ባህጉራችን ዘመን ኩነኔ :-
በስንትና ስንት ገጽታው
እስከዛሬ እየበለጨብን ጠባሳው ።

• •

አዞ — ስልት አመጣጥ
ምጣቱ
አዞ ስልት :—
ሰ—ተተ—ተተት ውስጥ ለውስጥ ።
ከጭንቅላቱ ጉዋሮ
ከዚያ ጉዋሮ ደሞ
ቀብሮ
ትምህርተ—ኅቡአት
እንደ ፈለገው ይፈጨው ፣ ብቻ ዱቄቱ ይምጣው እምነት።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• ተፈጥሮ ፍራቱዋ

ቀንዳውጣን ይመስል ቀንዳውጣን
ሲጠቀለል
እራሱን ከገዛ ውስጠቱ ሲያዉል ፣
በንዲያ—'ንዲያ ትስብስብ
ስብስብ — ስብስብ
ዘራሰብ ፣
በራሱ የሥልጣኔ ዐይነቱ ክንብንብ
ጉንብንብ
ከምላተ — ፍጥረቱ አባዕዶ ራሱን
እሹሩሩ — ሩሩ — ሩሩ
እየተንከባከበ ልጁን
እራስ መውደዱን ።
ምን አውሬ ሆኖ—'ንደሚወጣ እንጃለት
ከዚያ ክንብንባት ውስጥ
ጉንብንባት
እራሱ ያበጀው የሥልጣኔ ወጥመድ ።
እሱ ምጣት ነው ሞንቀት የነዛ
የነሰነሰ
እናት ተፈጥሮን ፍራቱዋን የቀሰቀሰ ።

• ፍቅር ገዳይ

"ፍቅር ሰው ገዳይ ነው" ሲሉ ሰምቶት
(የብድ ነገር) ፣
እና ገዳዩን ያገኘ መስሎት
አማሰለ
ፍቅር እራሱን አማሰለ
በሰላ ስለት ፤
እና ገደለ
ፍክ አበባ የሞቃ ርጋሞ አስመሰለ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• መሥፈሪያ

እንዴት ነበር እምትይዙዋቸው
ስትገዙዋቸው
እኒያን የቤቶቻችሁን ባሮች
የግሮቻችሁን ሥር ዕቃዎች
የሰብእናችሁን መሥፈሪያዎች ።

• ሙሾ ላማዴዉስ ሞዛርት

አልማዝ ንጥር
ጮራ ሥርሥር
ምራብ ጀምበር
አማዴዉስ
አዲዎስ ።

• •

ድምፅ ንጥር
ኅብረት ሥርሥር
ኖታ ድርድር
አማዴዉስ
አዲዎስ ።

• •

ሞት ዕረፍትህ
ራሱዋን ሆነህ
ሙዚቃን
ብርቅ ዕቃን
ብትሞትም አለህ ።

• •

አማዴዉስ ገናና
መቼ ትረሳና
ለዘላለማለሙ
በኅብረ — ሆታህ ጣዕሙ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• እንግዳዩት

የተጣለ ሸማ ትመስል
እንደ ዘበት
የመንገድ ዳር ጥቅልል ።

• •

ከጉልበቱዋ አሳርፋ
ክርኑዋን ፣
ሽቅብ ሰዳ
ክንዱዋን
ዐረፍ ከመዳፉዋ
አፉዋ ፤
ወዲያው ደሞ ትራስ
ላቀረቀረ—'ራስ ።

• •

እጥፍጥፌ
ሰፌ
(እጥንት)
ተጠመዛዛ የተቀመጠች ።
እምታስበውን እንጃ
ብቻ
እሱዋ
አለቦታዋ ነበረች አለቦታዋ
ላካባቢው እንግዳ ነበረች
በርግዋ
ችግርን በችግር የመግፋት ምጥ ።

• ጉልበተኛ የፈጠራት ዓለም

ከዚህ ወዲያ ከዚህ ፡ ከዚያ ወዲህ ብሎ
ተልሞ
ከትልሞው ላይ ጠመንጃውን አጋድሞ
እንዲያው እስቲ! እስቲ—'ንዳው ! እያለ
ዛቻ ከፖለቲካ እየቀላቀለ
እንዲያ እየቀላቀለ ከፋፈላት—'ንጂ
ጉልበተኛ
የሕይወት ሕይምቱዋ መጋኛ ፣
የኛ ምድራቱስ የኛ
ድሮ ወጥ ነበረች
ዐሥር መቶ ቦታ ያልተቆራረጠች ።
እና እንዲህ ሳይበለሻሽ ነገር
ተዙዋዙሮ
እሱዋስ በርግጥ ነበረች
ዘራሰብን ነጭ —ጥቁር ሳትለው ያቀፈች ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• የሂደት ዐይነት

ጉዞ ነው መቀመጥ ፤ መቀመጥ ጉዞ ነው
ጊዜ ባቡር እኛ ተሳፋሪዎቹ እየሆነው ።

• •

ቅድም ላሁን
አሁን ለሁዋላ ተቀምጠን
ያለፈም አልመሰለን
ጊዜ
አሳምሮ ሲያታልለን ።

• •

ጊዜ ግን አልፉዋል
ዕድሜም ጨምሩዋል
በደቂቃ
የጊዜ ቁዋቶች ዶቃ
ሥጋ—ካልም ተለውጡዋል ።

• •

ጉዞ ነውና ጉዞ ፤ መቀመጥ ጉዞ ነውና
ጊዜ ባቡር እኛም ተሳፋሪዎቹ ሆንና ።

• የፍቅር ጥያቄ

ምን ገመድ አስተሳሰረን ምን ገመድ
ምን የተደገፍነው ነበረ
የጋራ ግንድ?
ደርሶ መዋደድ ፤ መዋደድ ደርሶ !
ፍቅር መናገድ
እንዲህ እንደያዝነው
ከመሬት ተነሥተነው
እና በለውጡ ትተነው
ብዙ ብዙ በውድነት ይዘነው ከነበረው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• ያንድ አቅጣጫ ጩኸት

ዝቅ ወደ ታች— ታች እታች ዝቅ
ዝቅዝቅ
እኩል ለኩሉን ታዋፎ
እና ካፈር አሳክፎ
ግምባሩን
እና ደግፎ ፡ አበባ — ጉንጉኑን ።
እንደዚያው እንዳለ እንደዚያው
በዝቅ ዝቅ ዝቅታው
ኤደርግ ያለው
ለመቃብር ዐፈሩ ስጦታ
የድኅረ ግባተ—መሬት እንካታ ።
እሱን ስጦታ እንካ አለ
አስከሬኑን
ያፈር ውስጡን
እያረገፈ የምባ ቆሎ
አበባ — ጉንጉኑን ያጠጣ መስሎ
ምናልባት ሊያጸድቀው
ቢያጸድቀው ፡—
ቱግር ጨዋታ ፤ ጨዋታ ክስረት
እሬሳው —ንደሁ ቀና ብሎ ሳያሸትለት ።

• ክሥፍር ባሻገር

ያበቦች ቀለማምነት ያበቦች
ችቦ ድምቀት
ውበት ።
እሱ ውበት ነው እሱ ውበት
በፍኝ እማይሠፈር
እማይመተር ፤
በስንዝር እማይለካ
እማይነካ
እማይከነዳ ነገር እማይከነዳ
የውበት ረቂቅነት ዕዳ
ችግር
የሥፍር ባሻገር ምሥጢር ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• እርካታ

እየቀጠነ ሄደ እየቀጠነ
ሞብጥ እየመጠነ
ውፍረቱ ፡
እየተቀረደደ ቅርፊቱ
እየሰለለ ክርክራቱ
ግንድ ንጣቱ ።
ቀቅ—ቀቅ—ቀቅ!
እና ው—ድ—ድቅ!
ዛፍ ግርስስ!—ተገረሰሰ
ሣር — ቅጠሉን ይመሰሰ!
እና ቆሞ ያየው ጀመር
ደገፍ ያለው ደገፍ
ምሣሩን
እየጠራረገ ግምባሩን ።

• ኮዳ ቦጭ ቦጭ

በቀትር ፀሐይ ተመዝምዘው
በበረሃ ጉዞው
ምላስ ከትናጋ እያማጠጡ
ድርቀት ሲውጡ
አዩ ስታጉዋጉዋ ፡ ስታጉዋጉዋ
ኮዳ ፤
ኮዳ ቦጭ ቦጭ
የጀርባ ላይ ብድግ ቁጭ ።
ልጅ ትመስል ታዝላ
ኮዳዋ
እሱዋ እሬት—እሬት ፤ እኛ ሁዋላ—ሁዋላዋ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• የቦታ ጥያቄ

"የጥያቄ ምልክት ይመስላል አሉ" አሉ
ቅርጹዋ
አፍሪካ አህጉሩዋ ፡—
ከካይሮ እስከ ኬፕ ያለው መሬቱዋ ።

• •

እና የዚያ ጥያቄ ምልክት
ማለቂያው
ነጥቡ
ብረት ጥቁረት
ክቡ
"እየጋለ! እየጋለ! እየጋለ ሄደ አሉ" አሉ ።
"ፍም እየመሰለ ።"

• •

ልብ — ፍንቅል ማገዶ እየነደደበት
በነዲዱም እየተገለመጠበት
ዓለም
የምታመታችን ትልቁ ሕመም ።

• •

"ደሞ ፡ አንድ ሌላ ነገር አለ አሉ" አሉ
በነዲዱ የተገለመጡቱ
ሲያወሩ ።

"ወደ መሬት የተቃጣ ሽጉጥ ይመስላል አሉ" አሉ
ወደ መሬት የተቃጣ ሽጉጥ
ቅርጹዋ

ያፍሪካ አህጉሩዋ
ከካይሮ እስከ ኬፕ ያለው መሬቱዋ ።

• •

እና ፡ የዚያ ሽጉጥ አፈሙዙ
ብረት ጥቁረት
ምዙ
"አ!—ብሎ ቀርቱዋል አሉ" አሉ
ተገርሞ
"በቦታ ጥያቄ" ጉዳይ ታሞ ።

• •

"ከጋኑ ውስጥ ደሞ ፡ ጉርምርምታ ያሰማል አሉ" አሉ ፡
ኃይለኛ
ካሁን አሁን እያሰኘ ካሁን አሁን
ድም!—ድርግም!—ድምጥማጥ ሊያጠፋ
በቦታ ጥያቄ ላይ የደም ፍላት ሊደፋ ።

• •

ያ ከመሆኑ በፊት ግን ያ ከመሆኑ በፊት
ማን ይሙዋሙዋት!?
"የቦታን ጥያቄ" ፡ ጉዳዩን ይመልስ
የዘር መድሎውን በዘር እኩልነት ያድስ!?

• •

እሱ ነው ፡ "የቦታ ጥያቄው"
ቦታ ከነዘርማንዘሩ ፡ ዘርማንዘሩ የፈጠረው
ቦታ ሙሉ ቦተኞችን በጭብጥ መጥጢዎቹ ያስረገጠው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• ምርጫዬ ያለው ይመስል

እራሱ ከራሱ ጋራ ፣ ራሱ ጋራ ፣ የያዘ መስሎ
ሙግት

ግራ—ቀኝ አያይ ግራ—ቀኝ
አይገላመጥ
ወደ ሁዋላው አይመለከቅ
ወደ ፊት—'ፊቱ ብቻ ፣ ወደ ፊት—'ፊቱ
ሁዋላ ሁዋላው ፍየል ፤ ፍየል ሁዋላ ሁዋላው
ታብቶለት
በሆነ ስበት
ገመድ
ትች!—እየነዳለት ዘመድ
በንዲያ—'ንዲያ ሄዱ ፤ ሄዱ በንዲያ—'ንዲያ
ተያይዘው ።

እንድ ባልዲም በጃቸው :-
እንጥልጥላት
ውስጡ ብረድስት
ብረድስቱ ውስጥ ስለት ፤
የሆነ ክብሪት ደሞ እዚያው አብሮት
ተንተርሶት
ስለቱ
ጥቂት ነው የቀራቸው ከቦታቸው ሊደርሱ ።

• ድጉልጉል ደመና

የዛፎች ላይ—ላያቸውን ዘልቆ
ሽቅብ ርቆ
እስከዚያ ትልቅ ተራራ ፤
እሱንም ረግጦ
ጫፉን ፤
ያው ደመና
ድጉልጉላቱ
በትስግምግማቱ
ብርቅርቃቱ
ብንን—ድንግጥ እየተለኘበት ፍጥረቱ ።

• ቀለም ድምቄ

ትንስንስ—ንስንስ ፣ ንስንስ—ንስንስ
ስስ— የደስደስ— ስስ
ተውለብላቢ
የጠላት ዐይኖች ለብላቢ

• •

ደማቃ!—ሐር-'ራፊ— ደማቃ!
ብርቅ ዕቃ
የሰንደቅ ላይ ብጥቃ ።

• •

ነፋስ እሚያጨዋውታት
የኔ ብሉዋት ።
አራት ማዕዘን ቅድ
ቅንጣት
ዘላለም—ዓለም—ውድ ።

• •

አራት በኩሉዋን ክርክሜ
ያገር ዕድሜያችን መጠኑ ዕድሜ ።
እሰይ—እሰየው! ዐይነት ምልክት፡-
ብልጭልጩ!
ነፃነት እንቁልልጩ!

• •

ቀለማማ!—ቀለማማ!
ሥልሱዋን

http://ethioliberty.wordpress.com/

አርነቱዋዴ—ቡሄ—ቅይጣ
የሕልውናችን ግርማ—ምገስ ማማ ።

• •

የሱዋ ስሙዋ ስሜ
የምድራ—'ገሬ ፣ ምድራ—'ገሬ ጋሜ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• የዘመድ እንግዳ

እፍንጫዬ—ከንፈር ልጥፍጥፍ
እጅ—ጎመጅ እንከርፍፍ
ግንዳ—ግንዳም
ቅርንጫፋ—ቅርንጫፉም፡-
ሰው
የዘመድ ማሕል እንግዳው፡-
በተፈጥሮ ልጅነቱ ተዛምዶ
ከፍጥረት ነዶ ።
ዘረፀዋትን ይመስል
ሣር አብቅሎ
(ጸጉር)
ጥርስ ነቅሎ
እንደ ማንኛውም እንስሳ ነዋሪ፡-
በላዔ—ቅጠል
ሥጋ ተልትል
ሕይወቱን አሳዳሪ ሕይወቱን ።
እና ተዋጊ
ኑክሊዬራም ! ሠርነት ፈላጊ
በጣም
ማግሥትን ይመስል ልቡ አይታወቅም ።

• የዘራሰብ ጥገኛ

ነቀል—ነቀል
ካንጉቱዋ
ነቀል—ነቀል ።
• •

ሰደድ—መለስ
እራሱዋን
ሰደድ— መለስ ።
• •

ራመድ—ራመድ
እግሩዋ
ራመድ—ራመድ
ሄድ—ሄድ—ሄድ ።
• •

ወዲያው ደሞ ቆም
ኑና ትምም
በፍራት ስሜት፡-
ድንግጥ ድንግጥ
ገልመጥ ገልመጥ ።
• •

መሬት የያዘች ነገር
ኩንስንስ
ላባ ክብስብል
ርግብ
ምግብ ፈላጊ
እሚለቀም

ፈራ—ተባም ።

• •

በለቀማው ሰበብ
ታዴያንን
ሳብ—ሳብ
ማተቡዋ
ጥቁርቁር ጎብሩዋ ።

• •

በተሳስቦ ተዘረዘረ
እሱ
ስፋት ጨመረ
አንገትዋ ሲንጠራራ
ወደ ፊት
በሆነ ታርሞሽ ጉጉት ።

• •

ደሞ—ጎንደቅድመ
በፍራት
ብንን ብንን
እሽ! ያሉዋት ትመስል
ለጥቂት
ቱር! ልትል
ብር!
ዶርባ[illegible]ነገር ።

• •

ወዲያው ደሞ
ላፍታ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ተረጋግታ
እራሱዋን ወርወር
ወዳንዱ በኩል ፤
እና ጠጋ
ወደ ፊት
እሁንም ጠጋ
ጠቅ
መሬቱን ነካ
ምንቃሩዋን ሰካ ።

• •

የሆነ ነገር እነጣች
ጥሬ
ምናልባት ፍሬ
አንዲት
በለቀምኩ—ቃምኩ ጉጉት ።

• •

አይ ርግብ!
በጥገኝነት ነዋሪ
ከዘራሰብ
ረኀብ—ጥጋበን ተጋሪ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

በተዘርዝሮዋ ሕያውት ፡ ሕይወት በተዘርዝሮዋ
ተንያርድሮዋ
ቁልቁል
የተከለበሰ ውሃ መሰለች የተከለበሰ
ከጉርብጥብጥ መሬት የተላላሰ ።
እና በተላልሶው
ሲሄያው፡-
አልፍ ከቦታ ቦታ ፡ ከቦታ ቦታ አልፍ አለው
ወደ ፊት
እስከ—'ለተ—ሞቱ ጫፍ ፡
እየመራው ተዳፎቱ
የመሬቱ
ጉርብጥብጥ ዐይነቱ ።
በዚያ ጉርብጥብጣት ማይ ሂደቱ
የሕይወት
ወለምለም—ለምለም
ወዳንድ በኩል
ዘለምለም—ለምለም
ወደ ሌላው
እየቀጠለ ሂደቱ ፡ ሂደቱ እየቀጠለው
በወለም—ዘለሚው ፤ ለም—ዘለሚው
የሂደት-ሂደት ዐይነቱን አቀማመጡ እየወሰነው ።

ተመኘሁ አሁንም—'ሁንም ተመኘሁ
ቅርበት
ወደናት ፍጥረት
ዐይነ—ጥላዬ ይገፈፍልኝ ብዬ
ምላተ—እኔነቱዋን እንዳይላት
ችዬ
ባይነልቦናዬ ።
ማለት፡-
ተንጣሉዋን በርሬ
አግድም
ሰማየ ሰማያቱዋን መጥቄ
ሽቅብ
ዕመቄ—መሬቱዋን ሠርሥሬ
ቁልቁል
ምላተ—ፍጥረቱዋን እንዳይላት
እና እንዳውቃት
ዕንቅፋት ሳይሆን ቅንጣትነት
ኢምንትነት
ሰዋዊ ትንሽነት
ላይነልቦናዊ ፤ ነልቦናዊ ተዋውቆት ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• ማንሚነት

ባንድ አግጣጫዬ መንገድ ፡ ባንድ አግጣጫዬ ጎዳና
እስከ መሞቱ ፡ እስከ መበደኑ ሄደና
ያወ ና!
ያው !
ዕቅው
እንትኑ
በድኑ

ከፈን ብለው ባዲስ ቅዳጅ የጠቀለሉት ነገሩ
ከሆነ ከረጢት የተዶለው የሆነ ጥጥሩ ።
እና ፡ እሱን ጥጥር አንጋሎት
ከሆነ የሬሳ ሳጥን ጥሎት
በጀርባው
ምንም ሰማይ ላይታየው ።
ከዚያንን የሆነ ጉድጉዋድ መድረሻው
መጨረሻው

በመኖሪያ ቤትነት ተሰጠው ።
እና የዚያ ቤት ውስጥ ፡ የውስጥ ለውስጡ ጉዞው
የሱ መድረሻው
አዕምነት
አንዱን ከሌላው አይለዩ ማንሚነት ።
እና ኮለኮለ
ሳጥን—ከፈን—ዕርቃን—አጥንት እያሉ
ምስጥና—'ፈር ያመቃት ምስጥና-'ፈር
የነደሱ ያለ ሥራቸውን መርሐ—ግብር
የፈርፍር—ፈልፍል ሥራቸው ፡ የፈልፈል—ፈርፈር ።

• ምኒልክ ሐውልቱ

ምኒልክን እያስጨፈረ ፡ እያስጨፈረ ፡ እያስጨፈረ
ባስጨፍር—ጨፍር ነብረው አያውቁ ነበር ይመስል
ባካል
ከቶውንም
እነሁዋቸው ዛሬ እነሁዋቸው
ያይናችን ሥር ወረ
አባ—ዳኘውና ዳኘው ባውልታዊ መልካቸው
ከፍረካ—'ፋቃዋ ላይ ካፍረካ ጉባዋ ቆመው ።
እያተኮሩ ያንን ዝናማ ሜዳ
የጠላት ዕዳ
በይታቸው
አድዋ ትዝታቸው ።

• •

ፈረስ ዳኘው እየጨፈረ ፡ እየጨፈረ ፡ እየጨፈረ
ደንገላሳ
መስኖ ፈሰሳ
የፈረስ ግልቢያ—'ይነት ክለሳ ።
ጋማ ምቱንም እያስቆጠረ ፡ እያስቆጠረ
መደረቢያውንም እንጂ እያስነጠረ
የምኒልክን ፤
እና በንዴያ—'ንዲያ ሲታይ በንዲያ—'ንዲያ
ምኒልክ አባ—ዳኘው
ግርማው
የተራራ ላይ ፡ ተራራ ላይ ፡ ተራራ ላይ ተራራ ፡ ነው
እምላያው ።

• • •

http://ethioliberty.wordpress.com/

በምን አጋጣሚ ነበር ይሆን ምኒልክን ያየው
ያስተዋለው!?

(መቼም ባካል አይሆንም ፣ ባይነልቦናው ማለት)
(ባሳብ ተኮርኩሮት)

እንዲህ የተራራ ላይ ተራራ አስመስሎ ጉብያ-ረገው
ካፍሪካ—ፋፋዋ ላይ ፣ ካፍሪካ ጉባዋ ያቆመው
ያ ሐውልት ሠሪ

የሆነ ብረት በሆነ የሳት ምላስ መታሪ
ሕይወትን የሰጠ ያህል ፣ የጁን ሐውልት አናጋሪ
ስንከን ፈጣሪ ።
እሱ
በምን አጋጣሚ ነበር ይሆን ምኒልክን ያየው
ያስተዋለው!?

• •

የሐውልት ሐሳቡ መጀመሪያ ሲመጣለት
እሱ

መልክ አውጥቶ ሲያዝለት ፡—
ቀጨም!
ከብረት እሳት—ምላሱ ጫፍ ሲዘርቅለት
የሐውልት ቅርጹ ገጭ ብሎ ሲቆምለት
ከፊቱ

ምን ዐይነልቦናዊ መነሾ ነበር ይሆን ያነሣሣው
የሱን ፅንሰ—ሃየታ ከዕውነታ ያደረሰው !?

• •

እሱ ነበረ ጥያቄው ፣ ጥያቄው እሱ ነበር
የኔው

የዚያ ሐውልት ሥር ትንሽ ነገር
የሰውዬ
የተራራውን ላይ ተራራ ሳስተውለው ቀና ብዬ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

• ሰው

የሴሎች ሴሎች ክምችት
የቃላት ርችት ፡—
ቋንቅላታም ፣
በባሰ ይባስ ዐይነቱ ነገር ያዝ
ፍጥረትን ገዝ
ሳያሠልስ
እሱው አንጋሽ እሱው ንጉሥ ።

• ሙዳዬ-ቃላት

ሰባትካት ፡- የቅድመ ሥልጣኔ ዘመን ሰዎች ።
ስንከን ፡- Art
ዘራሰብ ፡- መላ የሰው ዘር ፤ ዘራዳም ።
ዩኒቨርስ ፡- Universe

http://ethioliberty.wordpress.com/

የሂደት ዐይነት 56
ሕይወት በተዘርዝሮዋ 72
የ ሕይወት ፍጥርቅታ 21

ልዩ—ነታ 12
ልጃገረድ 32

• •

መሥፈሪያ 52
ሙሾ ላማዩዉስ ሞዛርት . . . 53
ማንሚነት 74
ምርጫ ያለው ይመስል 64
ምኒልክ ሐውልቱ 75
ምኞት 35
ምኞት በዕራቁ 73

ሰባ ሰማኒያ 17
ሰው 78
ከ ሥፍር ባሻገር 59
በ ራሳጅ ቡና ቤት 19

ርእሶቹ በፊደል ተራ

ርእሳቸው ቀጥሎ የተዘረዘረው ግጥሞች ፤ ከሦስቱ በቀር ፣ ሁሉም አዲስ አበባ ውስጥ የተጻፉ ናቸው ። የአምስቱ ጉዳይ ግን እንደሚከተለው ነው ። "አመሻሽ ወርቅ" (አቴና አውሮፕላን ማረፊያ ፤ በትራንዚት መን ገደኛነት ፤ ኢአመ. አውሮፕላን ውስጥ) ፤ እርካታና ኮዳ ቦጫ ቦጫ" (ጎጃም) ።

ግጥም በተፀነሰበት ቦታና ሰዓት አይወለድም ። በፅንስነት ሲያድግ ቆይቶ በሌላ ቦታና ሰዓት ይወለዳል ። ከተወለደም በሁዋላ የሆነ መበጃጀት ያስፈልገዋልና ፤ ቆይቶ ነው ፤ በሰለ ተብሎ ሙጭርጭሩ በንጹሕ የሚመዘገብ ። ስለዚህ ፤ በማውጫው ውስጥና እዚህ የተሰጡት የፅንሰ ግጥሞቹ ቦታና ሰዓት በሞላ — ጎደ ላዊነት የተሰጡ መሆናቸው ይታወቅ ። ከዚህ ቀጥሎ ርእሶቹ እነሆ ፡—

http://ethioliberty.wordpress.com/

		ገጽ
	ቀለም ደምቲ	66
	ብርቃማሞች	30
የ	ቦታ ጥያቄ	62
የ	ተፈጥሮ ባላደራ	31
	ተፈጥሮ ብልጠቱዋ	25
	ተፈጥሮ ፍራቱዋ	50
	ነገር	24
የ	አመሻሽ ወርቅ	28
ዮ	አመሻሽ ፍለጋ	39
የ	አብሮ አብሮነት ጉዞ	13
ዮ	አንድ ሥልጣኔ ታሪክ	48
የ	አንድ አቅጣጫ ጨክት	58
እርካታ		60
እንግዳዊት		54

		ገጽ
	ከረምት	46
	ኮዳ ቦጭ ቦጭ	6
	መዲያ መዲህ	29
	ዘላለማለምን በግር	47
	ዘላለም ባብሮነት	41
የ	ዘመድ እንግዳ	68
	ዘራሲብ ጥያቄው	37
የ	ዘራሲብ ጥገኛ	69
	ድንልንል ደመና	65
	ንልበተኛ የፈጠራት ዓለም	55

http://ethioliberty.wordpress.com/

ገጽ

የ ፍቅር ዐይነት 40

ፍቅር ገዳይ 51

የ ፍቅር ጥያቄ 57

የ ፍጻሜው ባላይራ 42

* *

የ ፒያኖ ላይ ምጥ . 36



http://ethioliberty.wordpress.com/

"የውስጠት ሥርወቃል ወስጠ የሚለው ግዕዝ ቃል ነው ፤ቅርጹ ወይም አፍአዊ የቃል መልኩ ግን ፤ ግዕዝም አማርኛም ነው ..."

D AMH Say
Sayfu Matafariya
Westat 1988
ihvu 1
030102556100001